# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም፡-** ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.


## ዜና ዘገባ

**ጳጉሜን 5 ቀን 2003 ዓ.ም**

**የወያኔ ቡድን አሁንም እየታመሰ ነው፤**

**ብዙ ባለስልጣናት ከስልጣናቸው ተባረሩ፤**

**ዜጎች በሽብርተኝነት ስም እየታፈሱ ወደየት እንደሚወሰዱ አልታወቀም፤**

**ዳኞች በፀረ ሽብርተኝነት ህጉ ላይ መመሪያና ትዕዛዝ ሲሰጣቸው ሰነበተ፤**

ለ20 ዓመታት በህዝብና በሀገር ላይ ሲጫወቱ የኖሩት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት እርስ በርስ ስምምነት አጥተው እየተጠላለፉ ከመሆኑም በተጨማሪ ድምጽ በሌለው መሳሪያ መፋለም መጀመራቸው ተጋለጠ፡፡

ገና ስልጣን ላይ ከወጣ አጭር ግዜ የሆነው ለመለስ ፍፁም ታዛዥ የሆነው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት አለማየሁ አቶምሳ የተባለው ግለሰብ በኦህዴድ ውስጥ በፈጠረው የምንጠራ ዘመቻ የተበሳጩ የገዛ ባልደረቦቹ በታሸገ ውሀ የተቀመመ መርዝ ሰጥተውት ለከፋ ህመም ተዳርጎ እንደነበረ ምንጮቹ አጋልጠዋል::

ይሄው የኦሮሚያ ክልል ፕሬዝዳንት የሆነውና የመለስ ዜናዊ አዲሱ ባለሟል አባዱላን ከስልጣኑ እንዲወርድ በማስደረጉና እና ውስጥ ውስጡን ደጋፊዎችን ጭምር ከስልጣን እያባረረ እና እየመነጠረ ለእስር በመዳረጉ የተበሳጩት የኦህዴድ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ባዘጋጁት በመርዝ የተበከለ የታሸገ ውሀ በመጠታቱ ለከፋ ችግር ተዳርጎ እንደነበርና ለአራት ተከታታይ ወራት በውጭ ሀገር ህክምና አድርጎ የተመለሰ መሆኑን ምንጮቹ አብራርተዋል::

ምንም እንኳዋን ለአራት ወራት በውጭ ሀገር ህክምና አድርጎ የተመለሰ ቢሆንም አሁንም ሙሉ ጤነኛ እንዳልሆነ የጠቆሙት ምንጮቹ በተለይ ከመለስ ጋር ሆኖ በኦህዴዶች ላይ በምስጢር በሚሰራው ሸፍጥ የተነሳ በኦህዴድ ማዕከላዊ ምክር አባላትም ሆነ በሌሎቹ ዘንድ ከፍተኛ ጥላቻ ውስጥ እንደገባ ምንጮቹ ጨምረው ገልፀዋል::

በኦህዴድ ከፍተኛ ባለስልጣናት እምነት ያጣው መለስ ዜናዊ ከዚህ ቀደም ከነበሩት የክልሉ ፕሬዝዳንቶች ከአባዱላ ገመዳ ፤ከኩማ ደመቅሳ እና ከጁኔዲ ሳዶ በተለየ ሁኔታ ልዩ ጥበቃ ከቤተ መንግስት ተመድቦለት የሚጠብቁት ሲሆን መኖሪያ ቤቱም ጭምር በልዩ ጥበቃ ቁጥጥር ስር እንደዋለም ምንጮቹ ገልፀዋል::

በኦህዴድ ባለስልጣናት መሀከል ክፍተት እንዲፈጠርና እርስ በርስ ሽኩቻ ውስጥ እንዲገቡ እያደረገ ያለው መለስ ዜናዊ በደኢህዴን እና በብአዴን እንዲሁም በህወሀት ከፍተኛ የክልሉ ባለስልጣናት መሀከል እየገባ ለአገዛዙ በሚያመች ሁኔታ እያበጣበጠና እያከፋፈላቸው መሆኑንም ምንጮቹ አጋልጠዋል::

በቅርቡ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ብሎ ባዋቀረው ክልል ውስጥ በለስልጣናቱ መሀከል እርስ በርስ ንትርክ እና ጭቅጭቅ እንዲነሳ ተደርጎ ቁጥራቸው የበዛ ባለስልጣናት ከስልጣናቸው እንዲባረሩ ሲደረግ ገሚሱ ዘብጥያ ወርደዋል::

ለ14 ዓመታት ክልሉን በፕሬዝዳንትነት ሲያስተዳድር የነበረው ያረጋል አይሸሹም የተባለውን ግለሰብ የአይንህ ቀለም አላማረኝም በሚል አንስቶ የጥቃቅንና አነስተኛ ብሎ ያደራጃቸውን ወያኔ ወለድ የንግድ ሰራተኞች እንዲመራ ሲደረግ በምትኩ በክልሉ የአንድ ቢሮ ኃላፊ የነበረውን መሐመድ ናስር የተሰኘውን ማስቀመጡ የሚታወቅ ሲሆን ሰሞኑንም በዚህ ግለሰብ አማካኝነት ምንጠራ ማድረጉም ታውቆዋል::

የክልሉ ባለስልጣናት መሀከል መተማመንና መግባባት እንዲጠፋ ተደርጎ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ(ቤጉሕዴፓ) ምክትል ሊቀመንበርና የክልሉ ምክትል ፕሬዝዳንት ሰብስቤ ንሳኤ ጋስ የተሰኘውን ጨምሮ ቁጥራቸው የበዛ ባለስልጣናትን ያባረረ መሆኑም ታውቆዋል::

እርስ በርስ ስምምነት ጠፍቶ በመሀከላቸው ጉንተላ እንዲሰፍን ያደረገው የመለስ መዋቅር የተቃዋሚ ፓርቲ ደጋፊ ናቸው ሊባረሩ ይገባል ብሎ ለክልሉ ፕሬዝዳንት ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት የቤንሻንጉል ጉሙዝ የክልሉ አፈጉባዔ ሀብታሙ ኤካ ፤ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሰብስቤ ንሳኤ፤ የፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ታዬ ሀብቲ፤የስነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር ባይሳ ቤሲ፤የማክሮ ፋይናንስ ኃላፊ ዘላለም መገንባ ከኃላፊነታቸው እንዲነሱ ሲደረግ ሌሎችም በግምገማ ሰበብ ተወጥረው እንደሰነበቱ ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል::

የአዋሳ ከንቲባ የነበረውና ከመለስ ዜናዊ ሳይቀር ውዳሴና ምስጋና ሲቸረው የነበረው ሽብቁ ማጋኔ የተባለውን የወላይታ ተወላጅ አንስቶ በምትኩ የሲዳማ ብሔር ተወላጅ ሆነውን ዮናስ ዮሴፍን ለአዋሳ ከንቲባነት እንዲሾም ማድረጉ የመለስ የአገዛዝ ስልት በገዛ ባለስልጣናቱ ላይ ተለዋዋጭ እና ቋሚ ወዳጅ የሚለው ሰው እንደሌለ የሚያሳይ ነው ያለው የደረሰን ዘገባ በተለይ በወላይታ ብሔር ተወላጅ ባለስልጣናት ላይ ጠንከር ያለ ክትትል እያደረገ ከሌሎቹ የደቡብ ተወላጅ ባለስልጣናት ጋር በአይነ ቁራኛ እንዲጠባበቁ እያደረገ መሆኑንም ከአዋሳ የደረሰን ዘገባ ገልፆዋል::

በወላይታ ብሔር ተወላጆች ላይ ብዙ እምነት የሌለው የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊ ውስጥ ውስጡን እያደራጀ የተዳፈነና የተረሳውን የሎቄ ጭፍጨፋ ሊቀሰቅስ ይችላል በሚል ስጋት ብቻ ከአዋሳ ከንቲባነት ያነሳው ከመሆኑም ባሻገር እስከ አሁን ድረስ ስራ እንዳልተመደበም ከአዋሳ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል::

በሌላ ዜና የወያኔ ቡድን ከግዜ ወደ ግዜ በውስጡ በሚፈጥረው ስጋት የተነሳ የስልጣን እድሜ ሊያራዝም ይችላል በሚል ዜጎችን እያፈሰ ለእስር እየዳረገ መሆኑን በተለይ ከቅርብ ግዜ ወዲህ በስፋት እየሰራበት እንደሆነ ከተለያዩ አካባቢዎች የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ::

ሁለት የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮችን በሽብርተኝነት ሰበብ ለእስር ከዳረገ በሁዋላ እንደገና ከተለያዩ አካባቢዎች የኦነግ አባል ናችሁ እያለ ዜጎችን እያፈሰ ወዳልታወቀ ስፍራ እየወሰዳቸው መሆኑም ታውቆዋል::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በማስተማር ላይ የነበሩትና ከክፍል ውስጥ በደህንነትና መረጃ ሰራተኞች ታፍነው የተወሰዱት አቶ በቀለ ገርባ እና ከቢሮው ውስጥ በተመሳሳይ መልኩ በፌዴራል ፖሊሶች እየተዋከበ የተወሰደው አቶ ኦልባና ሌሊሳን ተከትሎ 29 ያህል የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ታፍሰው የደረሱበት አለመታወቁን ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል::

በዓመቱ መገባደጃ እና መጪው አዲስ ዓመትን መቀበያ ዋዜማ ላይ ከአዲስ አበባ ፤ከናዝሬትና ከሌሎች የኦሮሚያ ክልል አስተዳደሮች ዜጎች ከመኖሪያ ቤታቸውና ከስራ ቦታቸው እየተለቀሙ ወዳልታወቀ ስፍራ እየተወሰዱ ከመሆኑም በተጨማሪ በያሉበት እስር ቤቶች ከፍተኛ ድብደባ እየደረሰባቸው እንደሚገኝ የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል::

ከነሐሴ 21 ቀን 2003 ጀምሮ እየተስፋፋ የመጣው የኦሮሞ ብሔር ተወላጆች ላይ ያነጣጠረው የአፈሳ እርምጃ እስከ ዛሬዋ እለት ድረስ ቀጥሎ የሚገኝ ሰሆን ከናዝሬት ከአዲስ አበባ ፤ከምዕራብ ሸዋ፤

ከሰሜን ሸዋ እና ከሌሎችም ቦታዎች እየታፈሱ ተወስደው ወዳልታወቀ ስፍራ በመወሰዳቸው ቤተሰቦቻቸው ለከፋ እንግልት እና ስቃይ እየተዳረጉ እንደሚገኙ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

በቅርቡ ታፍሰው ከታሰሩት ዜጎች መሀከል

አበራ ደሜ ከምዕራብ ሸዋ፤

ጋቸና አራርሳ ከምዕራብ ሸዋ

ሀብታሙ ከምዕራብ ሸዋ

ጅራ አጀማ ከምዕራብ ሸዋ

ደረጀ አመና ከምዕራብ ሸዋ

ሞቱማ ፈየራ ከምዕራብ ሸዋ

በቀለ ኡርጌሳ ከምእራብ ሸዋ

ከበደ ዳዲ ከሰሜን ሸዋ

አብዲ ሶሪ ከምዕራብ ሸዋ

ሶኒሳ አበራ ከምዕራብ ሸዋ ተይዘው የደረሱበት አለመታወቁን የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

የዜጎቹን መታሰር አስመልክቶ የዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋቾች መግለጫ እያወጡ ሲሆን በተለይ ሁለቱ የመድረክ አመራሮች ለአምነስቲ ኢንተርናሽናል በቦረና እና በሌሎች ክልሎች ስለደረሰው ድርቅ እና ተያያዥ ጉዳዮች መረጃ በመስጠታቸው ብቻ ተይዘው እንደታሰሩ በመቃወም መግለጫ አውጥቶዋል፡፡

ለወያኔ የሚጠቅም ብቻ ተደርጎ የወጣውና አወዛጋቢ የሆነው የፀረ ሽብር ህጉ ተግባራዊ ከመሆኑ በፊት አምነስቲ ኢንተርናሽናልን ጨምሮ ሌሎች ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋቾች ጭምር ሲቃወሙት የነበረ መሆኑን የጠቆመው የደረሰን ዘገባ አሁንም ወያኔ ህጉን እየተጠቀመበት ያለው የዜጎችን መብት ለመጨፍለቅ እንደሆነ በይፋ ተቃውመው ገልፀዋል፡፡

ወያኔ በሀገሪቱ ብቸኛ እና አውራ ፓርቲ ሆኖ ለመቀጠል ካለው ፍላጎት የተነሳ የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎችን በሽብርተኝነት ስም እያስፈራራ ከመሆኑም ባሻገር አፍሶ እያሰረ አልፎ ተርፎ ውስጣችሁን አጥሩ እያለ ዛቻ መሰንዘሩ ብዙ ርቀት የማያስኬደው ጭፍን አመለካከት መሆኑ ታውቋል፡፡፡፡

በተለይ የአምነስቲ ኢንተርናሽናል ልዑካን ቡድን ኢትዮጵያን ጎብኝቶ ከወያኔ ባለስልጣናት ጋር ውይይት ለማድረግ የሞከረ ቢሆንም በአስቸኩዋይ ከሀገር እንዲወጡ በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ሰራተኞች ተገድደው ከወጡ ጥቂት ደቂቃ በሁዋላ ሁለቱ የመድረክ አመራሮች መታሰራቸው በእጅጉ እንዳሳሰበውም ድርጅቱ ጨምሮ ገልፆዋል፡፡

የአምነስቲ ኢንተርናሽናል የአፍሪካ ፕሮግራም ምክትል ዳይሬክተር እንዳሉት ከሆነ ጎብኚ ቡድናችን ከሀገር ተገድዶ እንዲወጣ በተደረገ ደቂቃዎች ውስጥ ሁለቱ የመድረክ አመራሮች መታሰረቸው በአጋጣሚ የተገጣጠመ ሳይሆን ሆን ተብሎ የተቀነባበረ ነው ሲሉም የወያኔን ገመና አጋልጠዋል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ በሽብርተኝነት ስም ዜጎችን እያፈሰ የሚገኘው የወያኔ ቡድን በጋዜጠኞች ላይም የማዋከቡን ዘመቻ በስፋት እንደቀጠለበት ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

በዑመድ አይመን አሳታሚ ስር በየወሩ የሚታተመው «የሙስሊም ጉዳዮች» የተሰኘው መፅሄት ዋና አዘጋጅ ጋዜጠኛ የሱፍ ጌታቸው ቅዳሜ ነሐሴ 21 ቀን 2003 ዓ.ም በሁለት የደህንነት ሰዎች ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠው ተገለፀ፡፡

በረከት እና ኤልያስ የተባሉ የደህንነት ሰዎች መስታወቱ ጥቁር ስቲከር በተለጠፈ መኪና ውስጥ አስገብተው ከእንግዲህ ብትፅፍ እስር ሳይሆን ሞት ይጠብቅሀል ..... አለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሙዋጋቾች ነን የሚሉትም ለአንድ ግዜ ቢያናፍሱልህ ነው ስለዚህ ደምህ በከንቱ እንዳይቀር መፃፍህን አቁም ሲሉም ዛቻና ማስፈራሪያ እንደሰነዘሩበት ታውቀዋል፡፡ምንም እንኩዋን የደህንነት ሰዎቹ በሽጉጥ እየጎሸሙ ቢያስፈራሩትም በህይወት እያለሁ ከመጻፍ ወደ ሁዋላ አልልም በማለት ምላሽ እንደሰጣቸውም ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ዜጎች በነፃነት የመኖር ህልውናቸው ፍጹም ባከተመበት በዚህ ግዜ ብዙ መከራና ስቃይ የሚደርስባቸው የነፃው ፕሬስ አባሎችን እያደኑ ከማሰርና ከመደብደብ አልፎ ተርፎ ሰሞኑን ደግሞ ማስፈራራት እና ዛቻ መሰንዘራቸው ስርዓቱ የለየለት ጭፍን አምባገነን እንደሆነ እያሳየ ነው ሲሉም ዜጎች በምሬት እየተናገሩ ይገኛሉ፡፡

በመጨረሻም ዜጎችን በሽብር ስም እያሰቃየ የሚገኘው የወያኔ ቡድን ከወረዳ እስከ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ድረስ ላሉ ዳኞች አዲስ መመሪያና ትዕዛዝ ሲሰጣቸው መሰነበቱ ታወቀ፡፡

በፀረ ሽብረተኝነት ላይ ጠንካራ መመሪያ እና ትዕዛዝ ሲሰጣቸው የሰነበቱት ዳኞቹ ማንኛውም በሽብር ስም ተከስሶ የመጣን ዜጋ ዋስ መስጠት እና በትንሹ ቅጣት መጣል እንዳማይቻል ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸው እንደነበር ለማወቅ ተችሎዋል፡፡

የደህንነት ባለሙያዎች እና ከፍተኛ የፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች ጭምር በሽብርተኝነት ላይ ስለሚወሰደው እና ስለሚሰጠው ፍርድ ውሳኔ ጠንካራ መሆን እንዳለበት መመሪያና ማስጠንቀቂያ ሲሰጣቸው እንደሰነበቱ የጠቆመው የደረሰን ዘገባ ብዙዎቹ ዳኞች በእኛ ሀገር ተጨባጭ ሁኔታ ሽብርተኛ ስለሌለ ህጉ ሊነሳ ይገባል ሲሉም ሲሞግቱ እንደሰነበቱም ዘገባው ገልፆዋል፡፡

ብዙዎቹ ዳኞች ሳያምኑበት በግዴታ መጪው ዓመት ዋነኛ ስራቸው በሽብርተኝነት ተብሎ በሚመጣ ፋይል ላይ ከባድ ውሳኔ እንዲያሳልፉ መሆኑ የተነገራቸው ሲሆን ቁጥራቸው ቀላል ያልሆኑት ግን ሳይስማሙ መውጣታቸውንም የደረሰን ጥቆማ ገልፆዋል፡፡

ስልጠናው ከነሐሴ 26 ቀን እስከ ጳጉሜ 3 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ለ7 ተከታታይ ቀናት የተሰጣቸው ሲሆን በተሰጣቸው የፀረ ሽብርተኝነት ኮርስ ላይ ብዙ አወዛጋቢና ግልጽ ሊሆኑ የሚገቡ ጥያቄዎችን አንስተው ሊመለስላቸው ባለመቻሉ ወደፊት በየቢሮዋችሁ በመጽሀፍ ተጠርዞ ይመጣላችሁዋል በሚል ያለስምምነት እንደተቁዋጨም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

በስልጠናው ወቅት አንዳንዱ ዳኞቹን እያባበሉ ሌላ ግዜ እያስፈራሩ እንደነበር የጠቆመው የደረሰን ዘገባ በተለይ ከደህንነት ቢሮ የሚመጡት ሰዎች በቁጣና በግዴታ መፈጸም አለባችሁ በሚል ላይ ብቻ የተመሰረተ ስልጠና ሲሰጡ እንደሰነበቱ አጋልጦዋል፡፡

የወያኔ ቡድን በአዋሽ ባንክ ኃላፊዎች ላይ የፈጸመውን የእስራት ዘመቻ ወደ ንግድ ባንክ ከፍተኛ ኃላፊዎች በማዛመት ከስራቸው ማባረር መጀመሩ ተጋለጠ፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብድርና የማገገሚያ ክፍል ዋና ኃላፊ የነበረው ክፍለፅዮን የተባለው ባለሙያ ለረዥም ዓመታት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ውስጥ ሲያገለግል የቆየና ነባር ብዙ ልምድ ያለው ሲሆን ድንገት ሳይታሰብ በደህንነት ሰራኞች ቢሮው እንዲታሸግ እና ከግቢ እንዲባረር መደረጉ ታውቆዋል፡፡

ህግና ደንብን ባልተከተለ አሰራር ህገ ወጥ በሆነ መልኩ የደህንነት ሰራተኞች ከቢሮው አስወጥተው የቆለፉበት እና ያሸጉት ከመሆኑም በተጨማሪ ሁለተኛ ወደዛ ግቢ እንዳይደርስ ጥብቅ ማስጠንቀቂያ እንደተሰጠውም ለማወቅ ችሎዋል፡፡

ነሐሴ 27 ቀን 2003 ዓ.ም ድንገት ከቢሮው አስወጥተው የግለሰቦችና የባንኩ ጠቃሚ አንገብጋቢና አጣዳፊ ውሳኔዎች የሚያስፈልጋቸው ዶኩሜንቶች እያሉ በጭፍን እና ህግና ስርዓት ባልተከተለ ሁኔታ ቢሮውን ማሸጋቸውም አስገራሚና ህግና ስርዓት በሀገሪቱ እየተደመሰሰ መሆኑን ያረጋገጠ ነው ተብሎዋል፡፡

የዚሁ ግለሰብ መባረርን ተከትሎ የድሬዳዋ የአትዮጵያ ንግድ ባንክ ስራ አስከያጅ የነበረው አክሊሉ ገብረስላሴም ከቦታው እንዲነሳና እጅግ ተራ ቦታ ላይ እንዲቀመጥ መደረጉ በባንክ ባለሙያዎች ላይ አዲስ የምንጠራና የማዋከብ ዘመቻ መጀመሩን የሚያመላክት ነው ተብሎዋል፡፡

ከቦታቸው ተነሱ ተብሎ በሰፊው ሲወራባቸው የነበሩት የህወሀት የበረሀ ታጋዮች እነ ታደሰ መሰረት የማዕከላዊ ምርመራን ለ19 ዓመታት ሲመራ ከቆየ በሁዋላ በአሁኑ ሰዓት ንግድ ባንክ እና ብሔራዊ ባንክን በስውር እየተቆጣጠረ እንደሚገኝም ለማወቅ ተችሎዋል፡፡